# ትንቢተ ኢዩኤል (52)

## ጥናት አንድ ኢዩኤል 1፡1-20

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር አምላካችን ምህረቱ የበዛ፣ ባለ ብዙ ጸጋና ፍቅሩ የማያልቅበት መልካም አምላክ እንደሆነ ልጆቻችንን ልናስተምራቸው እንደምንጥረው ያህል፤ ከዚያው ጋራ ደግሞ አምላካችን ጻድቅና እውነተኛ ፈራጅ እንደሆነ፤ በሃጥያት ላይ ፈጥኖ እንደሚፈርድም ጭምር አጥብቀን ልናስጠነቅቃቸው እንደሚገባን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…በእናንተ ዘመን ሆነ በአባቶቻችሁም ዘመን እንዲህ ዓይነት ነገር ሆኖ ያውቃልን? ይህንን ለልጆቻችሁ ተናገሩ፤ ልጆቻችሁ ለልጆቻቸው ይንገሩ፤ ልጆቻቸውም ለሚቀጥለው ትውልድ ይንገሩ።" ኢዩ 1፡2-3

1. ኢዩ 1፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ እግዚአብሄር አምላክ በነብዩ በኢዩኤል በኩል መልዕክቱን ሲያስተላልፍ በአድማጭነት ወይም ደግሞ መልዕክቱን እንዲሰሙለት የፈለጋቸው ሰዎች እነማን ነበሩ? በእነዚሁ ቁጥሮች ላይ ስትመለከት እግዚአብሄር እነዚህን አድማጮቹን በመልዕክቱ ውስጥ ጥያቄን ሲያቀርብላቸው እንመለከታለን፤ እነዚህ ሰዎች የተጠየቁት ጥያቄ ምን የምል ነበረ?
2. በቁ4-5 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ፤ በተለይም ደግሞ ቁ4ትን ስንመለከት እግዚአብሄር ከትውልድ ወደ ትውልድ ሁሉ እንዲተላለፍ የፈለገውና በሕዝቡ ላይ የደረሰበት አስከፊ ነገር ምንድነው? የምድሪቱን ሽማግሌዎችንና በአገሪቱ ላይ የሚኖረውን ህዝብ ሁሉ ማናገሩን አቁሞ፤ በቁ5 ላይ ደግሞ እግዚአብሔር መልዕክቱን ለሌላ አይነት አድማጮች ሲያስተላልፍ እናየዋለን፤ እነዚህ ሁለተኛዎቹ በኢዩኤል በኩል መልዕክት የሚመጣላቸው ሰዎች እነማን ናቸው?
3. ከቁ5 ጀምሮ እስከ ቁ12 ባሉት ክፍሎች ውስጥ የእግዚአብሄር ከተማ ስለምትገኝበት ሁኔታ እንዲያለቅሱ ወይም ደግሞ እንዲያዝኑ ሲነግራቸው እናያለን (ቁ5፣ ቁ8፣ ቁ9፣ ቁ11…)። በህዝቡ ሐጥያት ምክንያት በምድሪቱ ላይ የተከሰተው ይህ ሁኔታ በእግዚአብሄር ቤትና በአገልጋዮቹ ላይ ያስከተለው ነገር ምን ታያለህ? ቁ12 ላይ ስናነብ፤ ይህ ሁሉ በእግዚአብሄር ከተማና በእግዚአብሄር ሕዝብ ላይ የመጣው ከፍተኛ መቅሰፍት በሰዎች ሕይወት ላይ ያመጣው አንዱ ትልቅ ነገር ምንድነው?
4. እግዚአብሄር አምላክ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በቁ13-14 ላይ ስናነብ በምድሪቱ ላይ የመጣውን አስከፊ ሁኔታ ለመቀየር እንዲቻል በቅድሚያ ወይም በአንደኛ ደረጃ ለንስሃ የሚጠራው እነማንን ነው? እነዚህ ሰዎች ለንሥሃ የመጀመሪያ ተጠሪዎች ይሁኑ እንጂ ሁኔታው በእነርሱ ብቻ እንደማያቆም ከክፍሉ እንረዳለን። እነዚህ በመጀመሪያ ደረጃ ለንሥሃ የተጠሩት ሰዎች ቀጥለው ማድረግ የሚኖርባቸውና ከእግዚአብሄር የታዘዙት ነገር ምን እንዲያደርጉ ነው? አጠቃላይ ቤተ ክርስትያንን የበከለ ሐጥያት ሲኖር በመጀመሪያ ደረጃ በእግዚአብሄር ፊት ራሳቸውን በማዋረድ ምሳሌ መሆን ያለባቸው መሪዎችና የህዝብ አገልጋዮች መሆን እንዳለባቸው መዘንጋት አይገባም።
5. በበደልና በሃጥያታቸው ምክንያት በቁ12 ላይ ስንመለከት ደስታ ከሰው ልጆች ሁሉ እንደራቀ ሲናገር፤ ነገር ግን በጣም የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር በቁ16 ላይ ስናነብ ደግሞ ደስታና ተድላ በሙላት ሊገኝ ከሚገባበት ሥፍራ ጠፍቶ እንዳለ እናነባለን፤ ይህ ደስታና ተድላ ዘወትር ሊገኙበት ይገባል የሚባለው ሥፍራ ምን የት ነው?
6. ቁ17-20 ላይ ያለውን ሃሳብ ስናነብ በእግዚአብሄር ቤትም ጭምር ሳይቀር በምድሩ ሁሉ ላይ ያለውን በተለይም ድርቁንና የምግብን እጥረት አስመልክቶ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ተዘርዝረው ከምንመለከታቸው ሃሳቦች ውስጥ ጥቂቶቹን በመዘርዘር ተናገር። በነዚሁ ቁጥሮች ላይ ችግሮቹን በመዘርዘር ላይ እያለ በመሃል ቆም ብሎ በቁ19 ላይ አንድ የተለየ ነገር ሲያደርግ እናገኘዋለን፤ ይህ በዚህ ቁጥር ላይ ሲያደርግ የምታየው የተለየ ነገር ምንድነው?
7. እግዚአብሄር በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች እግዚአብሄር ለህዝቡ የሰራውን ድንቅ ሥራ ለልጆቻቸው እንዲነግሩ እንደሚያስጠነቅቃቸው እናውቃለን፤ መለስ ብለን ቁ3 ላይ ስናነብ፤ ሕዝቡ ለልጆቻቸው እንዲያስተላልፉት የፈለገው ሃሳብ ከዚህ ቀደም ከለመድነው መልዕክት የሚለየው በምን መንገድ ነው? አንተስ ለልጆችህ የምትናገረው የእግዚአብሄርን ፍቅር፣ ምህረትና በጎነት ብቻ ነው፤ ወይስ ደግሞ እግዚአብሄር የፍርድ አምላክም እንደሆነ ታስጠነቅቃቸዋለህ? እግዚአብሄር አምላካችን ምህረቱ ብዙ፣ ባለ ብዙ ጸጋና ፍቅሩ የማያልቅበት መልካም አምላክ መሆኑን መናገር አስፈላጊ ሲሆን፤ እውነተኛ በሃጥያት ላይ የሚፈርድ አምላክ መሆኑን መናገር ያስፈልጋል።

# ጥናት ሁለት ኢዩኤል 2፡1-32

የጥናት ዓላማ፡- "ልባችሁን እንጂ፣ ልብሳችሁን አትቅደዱ" በማለት ለይሁዳ እንደተናገረው፤ እግዚአብሄር ከህዝቡ የሚፈልገው የንስሃ ዓይነት ውጫዊና ለታይታ ያህል የሚደረግ ትያትር ሳይሆን፤ ትህትና በተሞላና በተሰበረ ልብ የሚደረግ እውነተኛ ንስሃን እንደሚፈልግ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አሁንም ቢሆን በጾም፣ በልቅሶና፣ በሃዘን በፍጹ ልባችሁ ወደ እኔ ተመለሱ ይላል እግዚአብሄር፤ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፣ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሄር ተመለሱ" ኢዩ 2፡12-13

1. ኢዩ 2፡1-32 በአንድነት ይነበብ፡፡ በምዕራፍ 1 ውስጥ የተከናወነና የሆነ ሁኔታን በማንሳት ሲያስጠነቅቅ፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ሊመጣ ያለን ሁኔታ በመጠቆም እግዚአብሄር አምላክ ህዝቡን ያስጠነቅቃል። ነብዩ በዚህ ክፍል በተለይ በቁ1 ላይ ሕዝቡን የሚያስጠነቅቃቸው ምንን አስመልክቶ ነው? እግዚአብሄር በተለያየ መንገድ ሕዝቡ የሚፈራና የሚንቀጠቀጥበትን ዓይነት መልዕክት ሲያስተላልፍ ነው የምናየው፤ ታዲያ የእግዚአብሄር ዋነኛው ዓላማ ሕዝቡን ማስፈራራትና ማስደንገጥ ነው ወይስ ይህንን የሚያደርግበት ዋነኛው ምክንያት ምንድነው ትላለህ?
2. ሊመጣ ያለውን ቀን አስመልክቶና ሊመጣ ያለውን ሰራዊት ሁኔታ በማስመልከት እግዚአብሄር ከቁ2 ጀምሮ ተናግሯል። ከቁ2 ብቻ በመነሳት ሊመጣ ያለውን ቀን አስመልክቶ የተነገሩትን የምታያቸውን ነገሮች፤ እንዲሁም ሰራዊቱን አስመልክቶ የተነገሩትን ሁለት ሃሳቦች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። ቁ3 ደግሞ ይህ የተነገረለት ሰራዊት ሊያደርግ ያለው ነገር ምን እንደሆነ አጠቃላይ ሃሳብ ሰፍሯል፤ ይህ ሰራዊቱ ሊያደርገው ያለውና በቁ3 ላይ ሰፍሮ የምናነበው ነገር ምንድነው?
3. ይህ የሚያስፈራ እያለ በዚህ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚናገረው የጌታ ቀን አስፈሪነቱ ለሰዎች ሁሉ ነው ወይስ ቀኑን መፍራት የማይኖርባቸው ሰዎች ይኖራሉ ብለህ ታምናለህ? በዚሁ አንጻር በኢዩኤል ምዕራፍ ሁለት ውስጥ ነብዩ ለምድሪቱ ህዝብ የእግዚአብሄርን ቀን ምንነት በሚያቀርብበት አቀራረብና፤ በ1ኛ ቆሮ 1፡8 ላይ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቅዱሳን ይህንኑ ቀን በሚያቀርብበት አቀራረብ መሃል የምትመለከተውን ልዩነት አስረዳ። ለአንተስ ይኽ ቀን የሚያስፈራ ነው ወይስ የሚናፈቅ?
4. በቁ8-9 ውስጥ ባለው ሃሳብ ብቻ ላይ በመመርኮዝ ስለዚህ ሰራዊት የተነገሩትን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር። በቁ3-11 ውስጥ በይሁዳ ላይ ሊመጣ ስላለው ሰራዊት አስከፊነት በሰፊው ይናገራል። እነዚህ ቁጥሮች ትኩረት ሰጥተን ስናነባቸው፤ ይኽ ሁሉ ታላቅ ሰራዊት የሚመራው በማን እንደሆነ ነው የምንመለከተው? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ።
5. በቁ13 ላይ ሕዝቡ ልባቸውን ሳይሆን ልብሳቸውን እንዲቀዱ በመናገር ሃጥያታቸውን በመናዘዝ ወደ አምላካቸው እንዲመለሱ ሕዝቡን ሲያበረታታቸው የእግዚአብሄርን ባህርያት በመጠቆም ነው፤ እነዚህ ኢዩኤል ስለ እግዚአብሔር በዚህ ቁጥር ላይ የጠቀሳቸው ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በቁ15-17 ውስጥ ጾምን እንዲያውጁና ሕዝብን ለንስሃ እንዲሰበስቡ ሲነገራቸው፤ ወደዚህ ጉባኤ እንዲመጡ ጥሪ እንዲደረግላቸው ከተጠሩት መሃል እነ ማንን ያካትታል?
6. በቁ15-17 ላይ የሚታየው የንስሃ ፍሬ በቁ18-27 ላይ ተዘርዝሮ እንመለከታለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከተዘረዘሩት የንስሃ ፍሬዎች መሃል ጥቂቶቹን በማንሳት ከወገኖች ጋራ ተወያዩባቸው። በኢዩ 1፡12 ላይ ያለውን ነገር ስናነብና፤ በዚህ በምዕ 2፡21 እና በ2፡23 ላይ ያለውን ሃሳብ ስንመለከት እውነተኛ ንስሃ በአማኝ ልብ ውስጥ ሊያስከትል የሚችለውን ስሜት እንረዳለን፤ ይህ በንስሃ ወደ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ሊመጣ የሚችለው ነገር ምንድነው?
7. ነብዩ ኢዩኤል በዚህ በኢዩ 2፡28-29 ላይ እግዚአብሄር ለህዝቡ የሚናገረውን የትንቢት ቃል፤ ሉቃስ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ላይ ይህንኑ ትንቢት ተቀብሎ በበሐዋ ሥራ 2፡17 ላይ ዳግመኛ ሲናገረው እንመለከታለን። በኢዩኤል ትንቢት ውስጥ የማናገኘው፤ ነገር ግን ሉቃስ በሐዋ ሥራ ላይ በተናገረው ሃሳብ ውስጥ ጊዜውን አስመልክቶ የተጠቀሰ ምን ሃሳብ ይታይሃል?
8. ቁ13 ላይ "ልባችሁን እንጂ፣ ልብሳችሁን አትቅደዱ" በማለት ይናገራል፤ እግዚአብሄር ለህዝቡ ይህንን እንዲያደርጉ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? በአንተስ ህይወት ልባቸውን ሳይሆን ልብሳቸውን ብቻ የሚቀዱ ሰዎች አጋጥመውህ ያውቃሉ ወይ? እግዚአብሄር ከህዝቡ የሚፈልገው የንስሃ ዓይነት ውጫዊና ለታይታ ያህል የሚደረግ ትያትር ሳይሆን፤ ትህትና በተሞላውና ከተሰበረ ልብ የመነጨ እውነተኛ ንስሃ እንደሆነ ልንገነዘብ ያስፈልገናል። በእኛ ዘመን ሰዎች ልብሳቸውን በመቅደድ ሊያስመስሉ እንደማይችሉ እናውቃለን፤ ታዲያ ዛሬስ ሰዎች ልባቸውን ሳይሆን ልብሳቸውን ብቻ ቀደዱ ማለት የምንችልበት ምን መንገዶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ሰፋ ያለ ውይይት ይደረግ።

# ጥናት ሶስት ኢዩኤል 3፡1-21

የጥናት ዓላማ፡- ምንም እንኳን አህዛብ የእግዚአብሄርን ቅዱሳን በመግፋትና በማስጨነቃቸው የሚያገኛቸው ምንም ነገር እንደሌለ ሆኖ ቢታይና የእግዚአብሄር አምላክ ፍርዱ የዘገየ ቢመስል፤ ርስቱ ለሆነው ለእስራኤል እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሄር ለህዝቡ በጽድቅ እንደሚፈርድ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አህዛብን ሁሉ እሰበስባለሁ፣ ወደ ኢዮሳፍጥም ሸለቆ አወርዳቸዋለሁ፣ ስለ ርስቴ፣ ስለ ህዝቤ፣ ስለ እስራኤል፣ በዚያ ልፈርድባቸው እገባለሁ፤ ምድሬን ከፋፍለዋልና፤ ሕዝቤንም በሕዝቦች መካከል በታትነዋልና።" ኢዩ 3፡2

1. ኢዩ 3፡1-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ባለው ክፍል ውስጥ ስናነብ፤ በዚያን ዘመን እግዚአብሄር በሁለት በተለያዩ ሕዝቦች ላይ ሊያደርግ እየተዘጋጀ ያለውን ሁለት ዓይነት ነገሮች እንመለከታለን፤ እነዚህ ሊያደርግ ያቀዳቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ነዋሪዎች ቢያንስ በሶስት ዓይነት ስሞች ሲጠራቸው እንመለከታለን፤ እነዚህ እግዚአብሄር የተጠቀመባቸው ሶስት ዓይነት መጠሪያዎች ምን ምንድናቸው?
2. በቁ4-8 ውስጥ ስናነብ እግዚአብሄር በነብዩ በኢዩኤል አማካኝነት ለጢሮስና ለሲዶና የሚያስተላልፈውን መልዕክት ስንመለከት፤ በገላ 6፡7 ላይ "አትሳቱ እግዚአብሄር አይዘበትበትም፤ ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና።" በማለት የእግዚአብሄር ቃል የሚናገረውን መመሪያ በተግባር ተፈጻሚ ሲሆን የምትመለከተው እንዴት ነው? አንተስ ወንድሜ በዚህች በተሰጠችህ እድሜ እየዘራህ ያለኸው ነገር ወደፊት ልታጭድ የምታስበውን ዓይነት ነገር ነው ወይ?
3. በቁ9-11 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ በምናነበው ሃሳብ ላይ እግዚአብሄር ከጠላቶቹ ጋራ እያደረገ ያለው ነገር አብዛኛውን ጊዜ የጦር መሪዎች ለጦርነት ሊወጡ ሲነሱ ከሚያደርጉት ነገር ጭራሽ የተለየ እንደሆነ ነው የምንመለከተው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር እያደረገ ያለው ነገር ከጦርነት አንጻር ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው? አህዛብ ለጦርነት በቁ9-11 ላይ ያለውን ያህል ዝግጅት አድርገው ከእግዚአብሄር ጋራ ለመዋጋት ቢመጡ እንኳን፤ በቁ12 እና 13 ላይ ከምንመለከተው የመጨረሻ ውጤቱ ምን እንደሆነ ነው የምናየው?
4. የፍርድ ቀን እየተባለ በቁ14-16 ላይ የሚነገረው ወይም ደግሞ እንደቀረበ የሚነገርለት "የእግዚአብሄር ቀን" በመባል ለሚታወቀው ቀን ምን ዓይነት እንደሆነ ለመግለጫነት ነብዩ ኢዩኤል በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተጠቀመባቸው ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። ይህ ቀን ለማንኛውም ሰው አስፈሪና አስጨናቂ እንደሆነ ቢታወቅም እንኳን ይህ ቀን የማያስፈራቸው ሰዎች ይኖራሉ፤ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ስትመለከት፤ እነዚህ ይህ ቀን የማያስፈራቸው ሰዎች እነማን ናቸው? አንተስ ያ የሚመጣው የእግዚአብሄር ቀን ከሚያስፈራቸው መሃል ነህ ወይስ በናፍቆት ከሚጠብቁት?
5. ነብዩ ኢዩኤል ቁ17ን ሲጀምር "ከዚያም" በማለት ነው የሚከፍተው። ይህ የነብዩ አነጋገር የትኛውን ጊዜ ሊጠቁም የፈለገ ነው የሚመስልህ? እግዚአብሄር ለህዝቡ በተለያዩ ቦታዎች እንደ አባትታቸው፣ ርስቱ እንደሆኑ፣ መንጋው እንደሆኑና እርሱም እረኛቸው እንደሆነ..ሌሎችንም አባባሎች በመጠቀም ከእነርሱ ጋራ ያለውን ግንኙነት ገልጿል፤ በዚህ ክፍል ውስጥስ እግዚአብሄር ራሱን ለህዝቡ እንደ ምን አድርጎ ነው ሲናገር የምናገኘው?
6. በቁ18-21 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ስታነብ፤ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የሚኖሩ እግዚአብሄር አምላካቸው የሆነላቸው ህዝቦች በሙሉ ይህንን እግዚአብሄር እየተናገረ ያለውን ነገሮች ከፍጻሜ መድረሳቸውን እንዲናፍቁት ሊያስመኛቸው የሚችሉ ምን ዓይነት ሃሳቦችን ትመለከታለህ? በእነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ስታነብ ለእግዚአብሄር ህዝብ የሚናፍቁት ጊዜ ቢሆንም በአንጻሩ ለእግዚአብሄር ጠላቶች ጊዜው አስፈሪ እንደሚሆን የሚጠቁሙን ሃሳቦች የትኞቹ ናቸው?
7. ቁ2-3 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት እግዚአብሄር በአህዛብ ላይ ሊፈርድ እንዳለ እንመለከታለን። በአህዛብ ላይ ለመፍረድ የተነሳበት ምክንያት ምን እንደሆነ ነው ከቁጥሮቹ የምንረዳው? የእግዚአብሄር ቅዱሳን ሲበደሉና ግፍ ሲደረግባቸው ተመልክተህ እንደ ነብዩ እንባቆም እስከመቼ ያልከበት ጊዜ አለ ወይ? ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሄር አምላክ ፍርዱ የዘገየ ቢመስልና አህዛብ በክፋታቸው እያየሉ መሄዳቸው ጥያቄ ቢሆንም፤ እግዚአብሄር ግን ለህዝቡ የሚፈርድበት ጊዜ እንዳለው እያልክ ዝም ያለ ቢመስልም እንኳን፤ በህዝቡ ላይ ለሚፈጸመው ግፍና በደል በጽድቅ የሚፈርድበት ጊዜ እንደሚመጣ መረዳት ያስፈልጋል።